# ሀገርም እናት ነች

ሶረኔ (ፍራንክፈርት)

በደምሽ ነጠብጣብ፣ ውሁድ - በስጋሽ ቁራሽ፣ የከፈንሽኝ፣
ባጥንትሽ ፍላጭ፣ ማገር - በጅማትሽ አውታር፣ ያቆምሽኝ፣
ያፈርሽን ወዝ፣ አልሰሽ - የእስትንፋስሽን ጋት፣ ያጠባሽኝ፣
ለመገበሪያሽ ዘር፣ እንድሆን - በኩዳድሽ፣ ያበቀልሽኝ፣
እንደ መስዋዕት ኮርማ፣ በግ - በስስት፣ ያሳደግሽን፣
ድሮ ገና ! ያማጥሽኝ - ጥንት ያኔ ! የወለድሽኝ፣
የማህጸንሽ አስኳል - ያንጀት ክፋይ፣ እኔው ነኝ።

እናት ኢትዮጵያ !!!
በዝክረ ሀበሻ፣ ስንክሳር - በያሬድ ዜማ፣ የተሾረብሽ፣
በሸሆቹ መንዙማ፣ ቅኝት - የሰላምን ቅኔን፣ የዘረፍሽ፣
ቀይ ከጥቁር፣ ዘር አጋምደሽ - በወግ በባህል፣ የተኳኳልሽ፣
የታሪክን ማግ፣ ፈትለሽ - በዘር ሐረግ፣ ያዳወርሽ፣
በጨረቃ ሱባኤ፣ መቁነን - በመስቀሉ ኪዳን፣ የቆረብሽ፣
አያል ዘመን፣ የተከበርሽ - አያል ዘመን፣ የመነንሽ፣
በቃል ኪዳኑ፣ የኖርሽ - የአጽመ አዳም፣ ስሪት ሆነሽ፣
የመስጊድ፣ ያድባራቱ፣........
የኪዳኑ ታቦት ጓዳ - የግማደ መስቀሉ፣ ማደሪያ ነሽ።

ድሮማ ! ያኔማ ! - ድፍን ዓለሙን፣ ያስደመምሽ፣
ከሙያም፣ ሐር ፈታይ - ከወላድም፣ በካር ነበርሽ፣
በሰንፔር አልማዝ፣ ያጌጥሽ - ያለምን ቀልብ፣ ያማለልሽ፣
በፍቅርሽ ንዳድ፣ ቀዝፈሽ - ስንት ሃያላንን፣ ያንበረከክሽ፣
ለጠላት መቅሰፍት፣ ሆነሽ - ውርደትን፣ ያከናነብሽ፣
የድንኳንሽን አውታር - በየብስ፣ በባህር የዘረጋሽ፣
ከጀግናም! ያናብስት ምድር - የነገስታት መንበር፣ ነበርሽ፣
በታሪክሽ የኮራሽ - በልጆችሽ ታፍረሽ፣ የኖርሽ።

ጥቂት ነገር፣ ልጠይቅሽ? - ዛሬስ፣ ምን ይላል ሆድሽ፣
ስንት ጸነስሽ፣ ስንት ወለድሽ - ስንት አመከንሽ፣ ስንት አሳደግሽ፣
ስንቴ አቦካሽ፣ ስንቴ ጋገርሽ - ስንቴ በላሽ፣ ስንቴ ተራብሽ፣
ስንቴ፣ ጾምሽ፣ ስንቴ ገደፍሽ - ስንቴ ታመምሽ - ስነቴ አገገምሽ፣
ሰንቴ አነባሽ፣ ስነቴ ሳቅሽ - ስንቴ ደላሽ፣ ስንቴ ማቀቅሽ፣
ዛሬም ይመዘበራል፣ ማጀትሽ - መቼ፣ ባለቤት ሆንሽ በቤትሽ፣
መቼ፣ ታበሰልሽና እንባሽ - መቼ፣ ደረስንልሽና ልጆችሽ፣
ዛሬም አላባራም፣ ከቶ ጣርሽ - ይቆጠራል፣ የጨለማው ዘመንሽ፣
ሁሌ ጭንቅ ነው፣ በቀየሽ፣......
ሁሌ ምጥ ነው በጓዳሽ - ቀንሽ ደርሶ፣ እስኪታወጅ ትንሳኤሽ።

እናት ኢትዮጵያ !!!
ሽሎችሽ፣ የመርገም አፈር - የሳጥናኤል ፈረስ፣ ከሆኑብሽ፣
ክብርና ዝናሽን፣ ገድፈው - የውርደት ማቅ፣ ካለበሱሽ፣
የለሊት መረዶ ገፊት፣ ቀማሽ - የቀን፣ ሙሾ አውራጅ ካረጉሽ፣
ሐዘንሽ፣ ቅጥ ያጣ ነው - ከቶ ለማን! ትነግሪያለሽ፣

የፍልሚየው ጎራ፣   ሰምሸ!.......
የፍልሚያው ጎራ ፣!ዝናሽ - ሟችም ገዳይም፣ ልጆችሽ፣
ለስንቱ ታነቢያለሽ? - ለስንቱስ፣ ታለቅሻለሽ፣
ተይው! መውለድሽ ይቅር - በከንቱ አይፍሰስ፣ ደምሽ፣
ይንጠፍ! ያጋተው ጡትሽ - ይምከን! ይቅር የዘር ቋትሽ፣
ከእንግዲህስ፣ አትቆዝሚ! - ሁኚ! እንደ እኩዮችሽ፣
መልክ እነደሁ፣ ይበቃሻል -  የዘር መድብል፣ ሥሪትሽ፣
ስምሽ! ለኛ ፈውስ ነው - መቅሰፍት! ለጠላቶችሽ፣
ያሀገር፣ የወገን፣ የዘር ብቅል - የቤት ያደባባይ ጉላላት፣
ማን ይገኛል እንደሃገር ! - ማንስ ይሆናል እነደናት፣
ግብሯ፣ ህያው ነው ዛሬም - ጣይቱ፣ ለኢትየዮጵያ ምስክር ናት።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!

አመሰግናለሁ!